የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን

ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ ክፍያዎች መመሪያ ቁጥር 1024/2017

መስከረም 2017

<u>የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ</u>

ባለሥልጣኑ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ማስፋት፣ በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና አሰራሮች የአገልግሎቶቹን የጥራት ደረጃ ማሻሻል እንዲሁም አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚያወጣውን ወጪ መሸፈን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት  አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ እና የመጠቀሚያ ክፍያ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም የሚኖረው ተገቢ ዋጋ ላይ የተመሰረተ መሆኑን እና ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለማስተዳደር፣ ፈቃድ ለመስጠት እና ለመቆጣጠር የሚያወጣውን ወጪ መሸፈን መቻሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፈቃድ እና የመጠቀሚያ ክፍያ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ሀብት ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም የሚኖረው ተገቢ ዋጋ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ፣ ከሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እና ከቁጥር ምደባ እና አስተዳደር እንዲሁም ከሬዲዮ ኮሙኒኬሽን እና ከቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት የሚሰበሰበውን የክፍያ መጠን በአግባቡ መወሰን በማስፈለጉ፤

ባለሥልጣኑ የሚያስከፍላቸውን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ ክፍያዎችን ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ መሰብሰብ የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ባለሥልጣኑ የሚስከፍላቸውን የፈቃድ እና የሬጉላቶሪ አገልግሎት ክፍያዎች ለተገልጋዮች ግልጽ እና ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የፈቃድ አገልግሎት እና የሬጉላቶሪ ክፍያዎች መመሪያዎች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ባለሥልጣኑ በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148 /2011 አንቀጽ 26(1)፣29(1)  እና 54(2) መሠረት ይህን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ ክፍያዎች መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ ክፍያዎች መመሪያ ቁጥር 1024/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1/ **"አስተዳደራዊ የማበረታቻ ዋጋ"** ማለት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ሃብት በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማበረታታት በባለሥልጣኑ ተግባራዊ የሚደረግ የዋጋ ተመን የማስቀመጥ ዘዴ ነው፤

2/ **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 3 መሰረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤

3/ **"ባንድ"** ማለት ተከታታይነት ያለው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አንድ ክፍል ነው፤

4/ **"ባንድዊድዝ"** ማለት በሬዲያ ፍሬኩዌንሲ ባንድ ወይም ቻናል ውስጥ የሚገኝ የስፔክትረም መጠን ወይም ስፋት ነው፤

5/ **"ቻናል"** ማለት መረጃን ለማስተላለፍ እና/ወይም ለመቀበል ጥቅም ላይ የሚውል የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ክፍል ነው፤

6/ **"መጨናነቅ"** ማለት ቁጥራቸው የበዛ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ተጠቃሚዎች ተቀራራቢ ወይም አጎራባች የሆኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረምን በተመሳሳይ ጊዜ ሲጠቀሙ የሚፈጠር ሁኔታ ነው፤

7/ **"የሀገር ውስጥ የፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት"** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የፈጣን መልዕክት ላኪ መልዕክት በመቀበል ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ የፈጣን መልዕክት ተቀባይ መልዕክት የመላክ ወይም የማድረስ አገልግሎት ነው፡፡

8/ **"ዱፕሌክስ ቻናል"** ማለት ኢንፎርሜሽን ለመቀበል እና ለመላክ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁለት የተለያዩ ፍሪኩዌንሲዎች ያሉት ቻናል ነው፤

9/ **"ዓለምአቀፍ የፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት"** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የፈጣን መልዕክት ላኪ መልዕክት በመቀበል ከኢትዮጵያ ውጪ ላለ የፈጣን መልዕክት

ተቀባይ የመላክ ወይም የማድረስ እና/ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ካለ የፈጣን መልዕክት ላኪ መልዕክት በመቀበል ኢትዮጵያ ውስጥ ላለ የፈጣን መልዕክት ተቀባይ መልዕክት የማድረስ አገልግሎት ነው፡፡

10/ **"አዋጅ"** ማለት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 ነው፤

11/ **"ከአንድ ማሰራጫ ወደ አንድ መቀበያ የሚደረግ ግንኙነት"** ማለት በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት ነው፤

12/ **"ከአንድ ማሰራጫ ወደ ብዙ መቀበያ የሚደረግ ግንኙነት"** ማለት ከአንድ ቋሚ ጣቢያ ወደ ብዙ ቋሚ ወይም ወይም ተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች የሚደረግ ግንኙነት ነው፤

13/ **"ስፔክትረም"** ማለት በ30 ኪሎ ኸርዝ እና በ300 ጊጋ ኸርዝ መካከል የሚገኝ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ነው፤

14/ **"የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ዋጋ"** ማለት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም የተወሰነ ክፍልን ለመጠቀም በየዓመቱ የሚከፈል ክፍያ ነው፤

15/ **"የስራ ቀናት"** ማለት ስራ የሚሰራባቸው ቀናት ሲሆን ቅዳሜ፣ እሁድ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ የሕዝብ በዓላት ተብለው የተሰየሙ ቀናትን አይጨምርም፡፡

16/ በአዋጁ እና በቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 792/2013 የተሰጡት ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 3. <u>አላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዋነኛ አላማ፡-

1/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና እድሳት ክፍያን መወሰን፤

2/ የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያን መወሰን፤

3/ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮች ምደባ እና መጠቀሚያ ክፍያን መወሰን፤ እና፣

4/ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ምደባ እና የመጠቀሚያ ክፍያ በመወሰን ውጤታማ እና ኢኮኖሚዊ የሆነ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀም እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ባለሥልጣኑ በሚሰጣቸው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃዶች፣ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃዶች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ምደባ፣ የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ እና ሌሎች ተያያዥ የሬጉላቶሪ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. አጠቃላይ መርሆች

ባለሥልጣኑ፡-

1/ ከኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እንዲሁም ከሌሎች የሬጉላቶሪ አገልግሎቶች የሚሰበሰበውን ክፍያ ያለአድልዎ ይሰበስባል፤

2/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ አገልግሎት ክፍያ መጠንን ለሕዝብ ግልጽ እና ተደራሽ ያደርጋል፤

3/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እንዲሁም የሌሎች ተያያዥ የሬጉላቶሪ አገልግሎት ክፍያዎች ከሌሎች ተመጣጣኝ ገበያዎች ወይም ሃገራት ክፍያዎች ጋር የተቀራረቡ እና የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ የዋጋ አተማመን ዘዴዎች እና ክፍያዎች

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ዋጋ አተማመን ዘዴ

## 6. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ የዋጋ አተማመን ዘዴዎች

1/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ክፍያ እና ተገቢ የጨረታ መነሻ ዋጋን የሚወስነው እንደ ሁኔታው የሚከተሉትን የአሰራር ስርዓቶች በተናጠል ወይም በጥምር መሰረት በማድረግ ይሆናል፡-

ሀ) በጨረታ እንደገና ቢመደቡ ከፍተኛ ተፈላጊነት ሊኖራቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡ የነባር ወይም የተጨናነቁ ፍሪኩዌንሲዎች ምደባ ክፍያ አስተዳደራዊ የማበረታቻ ዋጋን መሰረት በማድረግ ይወሰናል፤

ለ) ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸው ወይም መጨናነቅ ያለባቸው ባንዶች አዲስ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ምደባዎች ሲከናወኑ እንደ አስፈላጊነቱ ጨረታ ወይም ሌሎች በገበያ

ላይ የተመሰረቱ ስልቶች ፍሪኩዌንሲን ለመመደብ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚ ክፍያ አስተዳደራዊ የማበረታቻ ዋጋን መሰረት በማድረግ መወሰን አለበት፡፡

ሐ) ከፍተኛ ተፈላጊነት ወይም መጨናነቅ በማይኖርበት ወቅት፤ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አስተዳደር ማበራታቻ ዋጋን እና/ወይም ባለሥልጣኑ ፍሪኩዌንሲን ለማስተዳደር የሚያወጣውን ወጪ መሰረት በማድረግ ዓመታዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ብቻ እንዲከፈልባቸው ይደረጋል፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ክፍያ እና ተገቢ የጨረታ መነሻ ዋጋን ለመወሰን የሚከተሉትን ዘዴዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤

ሀ) በሌሎች ሀገሮች ወይም ገበያዎች የሚከፈሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያዎችን በመውሰድ ንጽጽር ማድረግ እና በገበያ ሁኔታዎች ላይ የሚታዩ ልዩነቶች የማስተካከያ ሁኔታዎች በመጠቀም፤ እና፣

ለ) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ባለቤቶች ገቢ እና የወጪ ሁኔታዎችን በመገመት፡፡

## 7. <u>መረጃ ስለመሰብሰብ</u>

1/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያን ለመወሰን የሚያስችሉ የሚከተሉትን አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ከሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ተጠቃሚዎች ይሰበስባል፤

ሀ) የማስተላለፊያዎች ወይም የተርሚናሎች ብዛት፤

ለ) የማስተላለፊያዎች ወይም የተርሚናሎች መገኛ ቦታ፤

ሐ) በእያንዳንዱ ማስተላለፊያ ወይም ተርሚናል ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ ፍሪኩዌንሲዎች ወይም ቻናሎች፤

መ) እያንዳንዱ ማስተላለፊያ ወይም ተርሚናል የሚጠቀመው ባንድዊድዝ፤ እና፣

ሠ) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፡፡

2/ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ተጠቃሚዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱ መረጃዎችን ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡለት በጠየቀ በሠላሳ (30) የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው።

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያዎች

### 8. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ ዓይነቶች

የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ የሚከተሉትን ክፍያዎች በተናጠል ወይም በጥምር አካቶ ሊይዝ ይችላል፡-

1/ የባለሥልጣኑን የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አስተዳደር ወጪዎች ለመሸፈን በየዓመቱ የሚከፈል የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያን፤

2/ የተወሰነ የሬዲዮ ፍሬኩዌንሲ ክፍልን ለተወሰነ የፈቃድ ዘመን ወይም ጊዜ ለመጠቀም በፈቃድ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በቅድሚያ የሚከፈል ወይም ባለሥልጣኑ በሚወስነው የክፍያ ጊዜዎች ተከፋፍሎ የሚከፈል ክፍያን፤

### 9. የሞባይል ፍሪኩዌንሲ ባንዶች ክፍያ

1/ ለሞባይል አገልግሎት የተመደቡ የእያንዳንዱ የፍሪኩዌንሲ ባንድ ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ ከታች በተመለከተው ቀመር እና በእያንዳንዱ የፍሪኩዌንሲ ባንድ የመነሻ ዋጋ እና ባንድዊድዝ መሠረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ** = የመነሻ ዋጋ X ባንድዊድዝ

ሠንጠረዥ 1፡ የሞባይል ፍሪኩዌንሲ ባንድ የመነሻ ዋጋ

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | የመነሻ ዋጋ (ብር/በሜጋ ኸርዝ/በዓመት) |
|---|---|
| 450 ሜጋ ኸርዝ | 967,200.00 |
| 600 ሜጋ ኸርዝ | 3,528,027.00 |
| 700 ሜጋ ኸርዝ | 3,337,785.00 |
| 800 ሜጋ ኸርዝ | 3,030,968.00 |
| 900 ሜጋ ኸርዝ | 2,780,934.00 |

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | የመነሻ ዋጋ (ብር/በሜጋ ኸርዝ/በዓመት) |
|---|---|
| 1800 ሜጋ ኸርዝ | 1,636,351.00 |
| 2100 ሜጋ ኸርዝ | 1,338,833.00 |
| 2300 ሜጋ ኸርዝ | 980,714.00 |
| 2600 ሜጋ ኸርዝ | 288,221.00 |
| 3500 ሜጋ ኸርዝ | 158,057.00 |

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ፈቃድ የተሰጣቸው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለሞባይል አገልግሎት ለተመደቡ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች የሚፈጽሙት ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረት ይሆናል፦

ሀ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 25% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

ለ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው ሁለተኛ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 50% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

ሐ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው ሶስተኛ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 75% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

መ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው 4ኛው ዓመት እና በቀጣይ የፈቃድ ዘመናት የአጠቃላይ ክፍያውን 100% እንዲከፍሉ ይደረጋል::

## 10. በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚደረግ ግንኙነት የሚመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች ክፍያ

1/ በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት የተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ ከታች በተመለከተው ቀመር እና በእያንዳንዱ የፍሪኩዌንሲ ባንድ የመነሻ ዋጋ፣ ባንድዊድዝ፣ የመጋራት ሁኔታ፣ የቦታ ሁኔታ፣ የሊንክ ሁኔታ እና የሊንክ ብዛት መሠረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፦

ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ = የመነሻ ዋጋ X ባንድዊድዝ X የመጋራት ሁኔታ X የቦታ ሁኔታ X የሊንክ ሁኔታ X የሊንክ ብዛት

የመጋራት ሁኔታ = 0.5

የቦታ ሁኔታ = 0.5

ሠንጠረዥ 2፡ በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት የሚያገለግል የፍሪኩዌንሲ ባንድ የመነሻ ዋጋ

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | የመነሻ ዋጋ ብር (በ2x1 ሜጋ ኸርዝ ሊንክ) |
|---|---|
| እስከ 1 ጊጋ ኸርዝ | 3,698.00 |
| ከ 1 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 3 ጊጋ ኸርዝ | 3,698.00 |
| ከ 3 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 5 ጊጋ ኸርዝ | 2,284.00 |
| ከ 5 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 10 ጊጋ ኸርዝ | 1,903.00 |
| ከ 10 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 17 ጊጋ ኸርዝ | 1,370.00 |
| ከ 17 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 24 ጊጋ ኸርዝ | 1,370.00 |
| ከ 24 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 30 ጊጋ ኸርዝ | 812.00 |
| ከ 30 ጊጋ ኸርዝ በላይ | 812.00 |

ሠንጠረዥ 3፡ የሊንክ ብዛት እና የሊንክ ሁኔታ

| የሊንክ ብዛት | የሊንክ ሁኔታ |
|---|---|
| እስከ 100 | 1.0 |
| ከ 101 እስከ 300 | 0.8 |
| ከ 300 በላይ | 0.6 |

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ፈቃድ የተሰጣቸው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በሁለት ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት

ለተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች የሚፈጽሙት ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረት ይሆናል፦

ሀ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 25% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

ለ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው ሁለተኛ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 50% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

ሐ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው ሶስተኛ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 75% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

መ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው 4ኛው ዓመት እና በቀጣይ የፈቃድ ዘመናት የአጠቃላይ ክፍያውን 100% እንዲከፍሉ ይደረጋል::

## 11. በቋሚ ጣቢያና ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚደረግ ግንኙነት የሚመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች ክፍያ

1/ በቋሚ ጣቢያና ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚኖር ግንኙነት የተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ ከታች በተመለከተው ቀመር እና በእያንዳንዱ የፍሪኩዌንሲ ባንድ የመነሻ ዋጋ፣ ባንድዊድዝ፣ ኔትወርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ እና የመጠቀሚያ ቦታ ሁኔታ መሠረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ለእያንዳንዱ ኔትዎርክ** = የመነሻ ዋጋ X ባንድዊድዝ X ኔትዎርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ X የመጠቀሚያ ቦታ ሁኔታ

ሠንጠረዥ 4: በቋሚ ጣቢያና ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚደረግ ግንኙነት የሚያገለግል የፍሪኩዌንኢ ባንድ የመነሻ ዋጋ እና የመጠቀሚያ ቦታ ሁኔታ

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | የመነሻ ዋጋ ብር (በ2x1 ሜጋ ኸርዝ ሊንክ) | የመጠቀሚያ ቦታ ሁኔታ |
|---|---|---|
| እስከ 1 ጊጋ ኸርዝ | 3,698.00 | 0.5 |
| ከ 1 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 3 ጊጋ ኸርዝ | 3,698.00 | 0.5 |

| የፍሪኩዌንሲ ባንድ | የመነሻ ዋጋ ብር (በ2x1 ሜጋ ኸርዝ ሊንክ) | የመጠቀሚያ ቦታ ሁኔታ |
|---|---|---|
| ከ 3 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 5 ጊጋ ኸርዝ | 2,284.00 | 0.5 |
| ከ 5 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 10 ጊጋ ኸርዝ | 1,903.00 | 0.5 |
| ከ 10 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 17 ጊጋ ኸርዝ | 1,370.00 | 0.5 |
| ከ 17 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 24 ጊጋ ኸርዝ | 1,370.00 | 0.5 |
| ከ 24 ጊጋ ኸርዝ በላይ እስከ 30 ጊጋ ኸርዝ | 812.00 | 0.5 |
| ከ 30 ጊጋ ኸርዝ በላይ | 812.00 | 0.5 |

ሠንጠረዥ 5: ኔትወርክ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ

| ኔትወርኩ የሚሸፍነው ቦታ ስፋት | ኔትዎርኩ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት ሁኔታ |
|---|---|
| አነስተኛ የቦታ ሽፋን ያለው ኔትወርክ ≤ 5 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 1 |
| ትልቅ የቦታ ሽፋን ያለው ኔትወርክ > 5 ኪሎ ሜትር ስኩዌር እና ≤ 600 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 2 |
| ሰፊ የቦታ ሽፋን ያለው ኔትወረክ > 600 ኪሎ ሜትር ስኩዌር እና ≤ 500,000 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 3 |
| ሀገራዊ ሽፋን ያለው ኔትወርክ > 500,000 ኪሎ ሜትር ስኩዌር | 30 |

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ፈቃድ የተሰጣቸው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በቋሚ ጣቢያና ከአንድ በላይ በሆኑ ቋሚ ጣቢያዎች መካከል ለሚደረግ ግንኙነት ለተመደቡ ፍሪኩዌንሲዎች የሚፈጽሙት ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረት ይሆናል፡-

ሀ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 25% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል።

ለ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው ሁለተኛ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 50% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል።

ሐ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው ሶስተኛ ዓመት የአጠቃላይ ክፍያውን 75% ብቻ እንዲከፍሉ ይደረጋል።

መ) የክፍያ መመሪያው ከጸናበት ዕለት ጀምሮ ባለው 4ኛው ዓመት እና በቀጣይ የፈቃድ ዘመናት የአጠቃላይ ክፍያውን 100% እንዲከፍሉ ይደረጋል።

## 12. ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች ክፍያ

ለብሮድካስት አገልግሎት ለተመደቡ የፍሪኩዌንሲ ባንዶች የሚከፈለው ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ በሚከተለው ሠንጠረዥ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ = የመነሻ ዋጋ X የማሰራጫ ብዛት**

ሠንጠረዥ 6: የብሮድካስቲንግ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ

<table>
<tr><th colspan="2">የማሰራጫ አይነት</th><th>የመነሻ ዋጋ ከተማ (ብር በእያንዳንዱ ማሰራጫ)</th><th>የመነሻ ዋጋ ገጠር (ብር በእያንዳንዱ ማሰራጫ)</th></tr>
<tr><td rowspan="3">አጭርና መካከለኛ ሞገድ</td><td>የግል/የንግድ</td><td colspan="2">20,225.00</td></tr>
<tr><td>የህዝብ</td><td colspan="2">14,160.00</td></tr>
<tr><td>የማህበረሰብ</td><td colspan="2">2,000.00</td></tr>
<tr><td rowspan="3">ኤፍ ኤም (የማሰራጫ ጉልበት <= 1 ኪሎ ዋት)</td><td>የግል/የንግድ</td><td>20,225.00</td><td>10,200.00</td></tr>
<tr><td>የህዝብ</td><td>14,160.00</td><td>7,100.00</td></tr>
<tr><td>የማህበረሰብ</td><td>2,000.00</td><td>1,000.00</td></tr>
<tr><td rowspan="3">ኤፍ ኤም (የማሰራጫ ጉልበት > 1ኪሎ ዋት)</td><td>የግል/የንግድ</td><td>28,300.00</td><td>14,160.00</td></tr>
<tr><td>የህዝብ</td><td>20,225.00</td><td>10,200.00</td></tr>
<tr><td>የማህበረሰብ</td><td>3,000.00</td><td>2,000.00</td></tr>
</table>

| የማሰራጫ አይነት | | የመነሻ ዋጋ ከተማ (ብር በእያንዳንዱ ማሰራጫ) | የመነሻ ዋጋ ገጠር (ብር በእያንዳንዱ ማሰራጫ) |
|---|---|---|---|
| ቴሌቪዥን (የማሰራጫ ጉልበት <= 1Kw) | የግል/የንግድ | 38,500.00 | 30,500.00 |
| | የህዝብ | 32,500.00 | 20,225.00 |
| | የማህበረሰብ | 4,045.00 | 3,000.00 |
| ቴሌቪዥን (የማሰራጫ ጉልበት> 1Kw) | የግል/የንግድ | 60,675.00 | 52,585.00 |
| | የህዝብ | 40,450.00 | 32,500.00 |
| | የማህበረሰብ | 6,068.00 | 4,045.00 |

## 13. ለመገናኛ ሬድዮ አገልግሎት የሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች ክፍያ

1/ ለመደበኛ የመገናኛ ሬድዮ ፍሪኩዌንሲ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሠረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ** = መነሻ ዋጋ X የሽፋን ሁኔታ X የባንድ ዊድዝ ሁኔታ X የሬድዮኖች ብዛት ሁኔታ

**መነሻ ዋጋ** = 810 ብር

2/ የግል ወይም የህዝብ ትራንክ ኔትዎርክ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሠረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ** = መነሻ ዋጋ X የባንድ ዊድዝ ሁኔታ X የሬድዮኖች ብዛት ሁኔታ X የአጠቃቀም አይነት

**መነሻ ዋጋ** = 400 ብር

**የአጠቃቀም አይነት፡** ለግል = 1

ለህዝብ = 0.5

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ለተገለጹት የመደበኛ የመገናኛ ሬዲዮ እና ለግል ወይም ለህዝብ ትራንክ ኔትዎርክ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ስሌት የሽፋን ሁኔታ፣ የባንድዊድዝ ሁኔታ እና የሬዲዮኖች ብዛት ሁኔታ ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ በተገለጸው መሠረት መወሰድ አለበት፡-

ሠንጠረዥ 7: የሽፋን ሁኔታ

| የሽፋን መግለጫ | የሽፋን ሁኔታ |
|---|---|
| እስከ 15 ኪ.ሜ ለሚደርስ ሽፋን | 1 |
| እስከ 30 ኪ.ሜ ለሚደርስ ሽፋን | 2.5 |
| እስከ 60 ኪ.ሜ ለሚደርስ ሽፋን | 5 |
| ሀገራዊ ሽፋን ላለው | 15 |

ሠንጠረዥ 8: የባንድዊድዝ ሁኔታ

| የተመደበ ባንድ ዊድዝ | ባንድዊድዝ ሁኔታ |
|---|---|
| 3 ኪሎ ኸርዝ ወይም 6.25 ኪሎ ኸርዝ ወይም 12.5 ኪሎ ኸርዝ ወይም 20 ኪሎ ኸርዝ ሲምፕሌክስ ቻናል | 1 |
| 3 ኪሎ ኸርዝ ወይም 6.25 ኪሎ ኸርዝ ወይም 12.5 ኪሎ ኸርዝ ወይም 20 ኪሎ ኸርዝ ዱፕሌክስ ቻናል | 2 |
| 25 ኪሎ ኸርዝ ሲምፕሌክስ ቻናል | 1.25 |
| 25 ኪሎ ኸርዝ ዱፕሌክስ ቻናል | 2.5 |

ሠንጠረዥ 9: የሬዲዮኖች ብዛት ሁኔታ

| የሬድዮኖች ቁጥር | የሬዲዮኖች ሁኔታ |
|---|---|
| እስከ 10 ሬድዮኖች | 1 |
| ከ 11 እስክ 35 ሬድዮኖች | 2 |
| ከ 35 ሬድዮኖች በላይ | 3 |
| ለሀገራዊ ሽፋን ፍሪኩዌንሲው/ዎቹ በብቸኝነት ሲመደብ/ቡ | 4 |

## 14. ለኤሮናቲካል እና ለማሪታይም አገልግሎት የሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች ክፍያ

ለኤሮናቲካል እና ማሪታይም አገልግሎት ለሚውል ፍሪኩዌንሲ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሠረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ** = መነሻ ዋጋ X የባንድ ዊድዝ ሁኔታ

**መነሻ ዋጋ** = 810 ብር

ሠንጠረዥ 10: የባንድ ዊድዝ ሁኔታ

| የተመደበ ባንድ ዊድዝ | የባንድዊድዝ ሁኔታ |
|---|---|
| 3 ኪሎ ኸርዝ | 1.5 |
| 6.25 ኪሎ ኸርዝ ወይም 12.5 ኪሎ ኸርዝ | 2 |
| 25 ኪሎ ኸርዝ | 2.5 |

## 15. ለሳተላይት የምድር ጣቢያ አገልግሎት የሚውሉ ፍሪኩዌንሲዎች ክፍያ

ለሳተላይት የምድር ጣቢያ አገልግሎት ለሚውል ፍሪኩዌንሲ ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ መጠቀሚያ ክፍያ ከዚህ በታች ባለው ቀመር መሰረት ተሰልቶ መከፈል አለበት፡-

**ዓመታዊ የፍሪኩዌንሲ ክፍያ** = መነሻ ዋጋ X ባንድ ዊድዝ

**መነሻ ዋጋ** = 365 ብር በሜጋ ኸርዝ

## ክፍል ሦስት

## የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ

## 16. የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (8) መሰረት ለሚሰጠው የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ያስከፍላል፡፡

2/ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ወይም የሚመረቱ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ብዛት ከአንድ በላይ ቢሆንም ለተመሳሳይ ሞዴሎች የሚከፈለው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ ለአንዱ መሣሪያ የሚከፈለው የክፍያ መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

3/ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ወይም የሚመረቱ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ሞዴል የተለያየ ከሆነ ለቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚከፈለው ክፍያ በእያንዳንዱ የተለያዩ ሞዴሎች ሆኖ ለአንዱ መሳሪያ የሚከፈለው ክፍያ ይሆናል፡፡

## 17. <u>የመሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ክፍያ መጠን</u>

1/ ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚከተሉትን ክፍያዎች ያስከፍላል፡፡

| ቁጥር | የመሣሪያው ስም | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለግለሰብ መጠቀሚያ) (በብር) | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለተቋም እና ለንግድ ድርጅት) (በብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | የተርሚናል መሳሪያዎች (የደንበኞች የግል መገልገያ መሣሪያዎች) | | |
| | • መደበኛ ስልክ (ባለገመድ/ገመድ አልባ)<br>• የሞባይል ቀፎ<br>• የፋክስ ማሽኖች<br>• የሲዲኤምኤ ገመድ አልባ የስልክ ቀፎ<br>• የአይፒ ስልኮች<br>• ሲም ካርድ የሚወስድ አይፓድ/ታብሌት<br>• ሲም ካርድ የሚወስድ፣ ብሉቱዝ ሞጁል እና የዋይፋይ ሞጁል ያለው ላፕቶፕ | 100.00 | 500.00 |

| ቁጥር | የመሣሪያው ስም | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለግለሰብ መጠቀሚያ) (በብር) | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለተቋም እና ለንግድ ድርጅት) (በብር) |
|---|---|---|---|
| | • የሞባይል ዋይፋይ ራውተሮች<br>• 3G/4G/5G የሞባይል መጠቀሚያ USB Dongle<br>• ፖስ ማሽን<br>• የሳተላይት ሞባይል ስልኮች እና<br>• ሌሎች መሰል መሳሪያዎች | | |
| 2 | አነስተኛ ኃይል/ጉልበት ያላቸው መሣሪያዎች (የአጭር ርቀት መሣሪያዎች) | | |
| | • ዋይ ፋይ፣ ብሉቱዝ ሞጁሎች<br>• የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መለያ መሳሪያዎች<br>• ቴሌሜትሪ እና የትእዛዝ ሞጁሎች<br>• ገመድ አልባ ማይክሮፎኖች<br>• የርቀት ቁልፍ አልባ የመግቢያ እና ተደራሽነት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች<br>• ተሽከርካሪ እንዳይንቀሳቀስ ማድረጊያ መሳሪያ<br>• የእንቅስቃሴ መከታተያ መሳሪያ<br>• ገመድ አልባ ማንቂያ ሲስተም | 100.00 | 500.00 |

| ቁጥር | የመሣሪያው ስም | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለግለሰብ መጠቀሚያ) (በብር) | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለተቋም እና ለንግድ ድርጅት) (በብር) |
|---|---|---|---|
| | • ገመድ አልባ የቅርብ አካባቢ ኔትዎርክ መዳረሻ መሣሪያ<br>• ገመድ አልባ የቅርብ አካባቢ ኔትዎርክ ሞጁል/ ካርዶች<br>• በሰው አካል ላይ ወይም ውስጥ ተገጥመው ድጋፍ የሚሰጡ የሕክምና መሳሪዎች እና<br>• ሌሎች መሰል መሣያዎች | | |
| 3 | የጥሪ ማዞሪያ መሣሪያዎች/የግል ቅርንጫፍ ማዞሪያ መሣሪያዎች | | |
| | • እስከ 16 የሚደርሱ የውስጥ መስመሮች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 500.00 |
| | • ከ 16 በላይ እስከ 32 የውስጥ መስመሮች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 550.00 |
| | • ከ 32 በላይ እስከ 64 የውስጥ መስመሮች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 600.00 |
| | • ከ 64 በላይ እስከ 128 የውስጥ መስመሮች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 650.00 |
| | • ከ128 በላይ እስከ 256 የውስጥ መስመሮች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 700.00 |

| ቁጥር | የመሣሪያው ስም | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለግለሰብ መጠቀሚያ) (በብር) | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለተቋም እና ለንግድ ድርጅት) (በብር) |
|---|---|---|---|
| | • ከ256 በላይ የውስጥ መስሮች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 750.00 |
| 4 | የአይቲ ኔትዎርክ መሣሪያዎች | | |
| | • ሞደም፣ ስዊች፣ ራውተር፣ ሰርቨር እና መሰል መሣሪያዎች | 200 | 500.00 |
| 5 | የሞባይል ሬዲዮ እና ዋና የኔትዎርክ መሳሪያዎች | | |
| | • BSCs፣ MSCs፣ BTS፣ Node B፣ eNodeB፣ gNodeB (gNB)፣ ማይክሮዌቭ ሬዲዮ፣ ኮር ስዊች፣ ጌትዌይ እና መሰል መሳሪያዎች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 3,000.00 |
| 6 | የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያዎች | | |
| 6.1 | • ኤችኤፍ፣ ቪኤችኤፍ፣ ዩኤችኤፍ ሬዲዮ<br>• ከአንድ ማሰራጫ ወደ ብዙ መቀበያ የሚያሰራጭ ሬዲዮ<br>• ከአንድ ማሰራጫ ወደ አንድ መቀበያ የሚያሰራጭ ሬዲዮ | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 500.00 |
| 6.2 | • አማተር ሬዲዮ/የሲቲዝን ባንድ ሬዲዮ እና | 100.00 | 250.00 |

| ቁጥር | የመሣሪያው ስም | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለግለሰብ መጠቀሚያ) (በብር) | የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ (ለተቋም እና ለንግድ ድርጅት) (በብር) |
|---|---|---|---|
| | • ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች | | |
| 7 | የምድር የሳተላይት ተርሚናል | | |
| | • ቪሳት<br>• የሳተላይት ሞደም<br>• የሳተላይት ራውተር እና<br>• ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች | መሣሪያው በግለሰብ እንዲገባ አይፈቀድም | 750.00 |

## ክፍል አራት

## የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ

### 18. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ እና በቴሌኮሙኒኬሽን ፍቃድ መመሪያ ቁጥር 792/2013 መሠረት ለሚሰጠው ፈቃድ ተገቢውን የፈቃድ እና የእድሳት ክፍያ ያስከፍላል፤

2/ ፈቃዱ የጠፋበት፣ የተበላሸበት፣ ወይም በሌላ ምክንያት ፈቃዱ እንዲተካለት የሚጠይቅ ባለፈቃድ ጥያቄውን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ እና ለዛ ፈቃድ የተቀመጠውን የማመልከቻ ክፍያ ወይም ፈቃዱ የማመልከቻ ክፍያ የማይከፈልበት ከሆነ ብር አምስት መቶ (500.00) በመክፈል ምትክ ፈቃድ ማግኘት ይችላል።

3/ ባለፈቃዱ ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀበት ምክንያት ባለሥልጣኑ በፈጸመው ስህተት ከሆነ እርማት ለማድረግ ወይም ምትክ ፈቃድ ለመስጠት ባለፈቃዱ ክፍያ እንዲፈጽም አይጠየቅም።

## 19. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ክፍያ መጠን

1/ ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ የሚከተሉትን ክፍያዎች የሚያስከፍል ይሆናል፤

ሀ) የፈቃድ ዘመናቸው ከአንድ (1) ዓመት በላይ ለሆኑ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃዶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤

| ተ/ቁ | የፈቃድ አይነት | የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ (ብር) | የፈቃድ ክፍያ (ብር) | ዓመታዊ አስተዳደራዊ ክፍያ (ብር) | የፈቃድ ዘመን (በዓመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 2,500.00 | 5,000,000.00 | 1% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 10 ዓመት |
| 2 | የዳታ ማዕከል አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 2,500.00 | 500,000.00 | 0.5% ከአጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ላይ (በብር) | 10 ዓመት |
| 3 | የሁሉን አቀፍ አገልግሎት ተደራሽነት ግዴታ ያለበት የህዝብ ብሔራዊ የፖስታ አገልግሎት ፈቃድ | 5,000.00 | 250,000.00 | 100,000.00 | 15 ዓመት |

ለ) የፈቃድ ዘመናቸው አንድ (1) ዓመት ሆኖ በየዓመቱ ፈቃዳቸው መታደስ ላለበት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃዶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ስም | የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ (ብር) | የፈቃድ ክፍያ (በብር) | የፈቃድ እድሳት ክፍያ (በብር) | የፈቃድ ዘመን (በዓመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሆስቲንግ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 300.00 | 35,000.00 | 20,000.00 | 1 ዓመት |
| 2 | የጥሪ ማዕከል አገልግሎት ፈቃድ፤ | 300.00 | 35,000.00 | 20,000.00 | 1 ዓመት |
| 3 | የቴሌኮሙኒኬሽን ተጨማሪ አገልግሎቶች ፈቃድ፤ | 300.00 | 35,000.00 | 20,000.00 | 1 ዓመት |
| 4 | የመሠረተልማት አቅርቦትን ያላካተተ የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ፤ | 300.00 | 35,000.00 | 20,000.00 | 1 ዓመት |
| 5 | ዓለም አቀፍ የሳተላይት የግል ሞባይል ግንኙነት አገልግሎት ፈቃድ፤ | $ 500.00 (በአሜሪካ ዶላር) | $ 5,000.00 (በአሜሪካ ዶላር) | $ 5,000.00 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |
| 6 | የግል ኔትዎርክ እና እርስበርስ የተያያዘ ለተወሰነ ተጠቃሚ ቡድን | $ 500.00 (በአሜሪካ ዶላር) | $ 5,000.00 (በአሜሪካ ዶላር) | $ 5,000.00 (በአሜሪካ ዶላር) | 1 ዓመት |

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ስም | የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ (ብር) | የፈቃድ ክፍያ (በብር) | የፈቃድ እድሳት ክፍያ (በብር) | የፈቃድ ዘመን (በዓመት) |
|---|---|---|---|---|---|
| | ግንኙነት የሚውል ኔትወርክ ፈቃድ | | | | |
| 7 | የውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ፤ | 300.00 | 1,500.00 | 1,000.00 | 1 ዓመት |
| 8 | የውጭ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ፈቃድ፤ | 300.00 | 50,000.00 | 35,000.00 | 1 ዓመት |
| 9 | ዓለም አቀፍ የፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት ፈቃድ | 300.00 | 50,000.00 | 35,000.00 | 1 ዓመት |
| 10 | የሃገር ውስጥ ፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት ፈቃድ | 300.00 | 10,000.00 | 5,000.00 | 1 ዓመት |
| 11 | የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኢንቬስትመንት ፈቃድ | 300.00 | 600.00 | ተፈጻሚ የማይሆን | ተፈጻሚ የማይሆን |

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው ቢኖርም የተገለጹት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የክፍያ መጠን የተጣመረ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ያለው ኦፕሬተርን አይመለከትም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው ቢኖርም በነጠላ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የፈቃድ አይነቶችን አንድ ላይ የሚይዝ አጠቃላይ ፈቃድ ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ሊሰጥ ይችላል፡ -

ሀ) የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ የወሰደ ባለፈቃድ የዳታ ማዕከል አገልግሎት፣ የሆስቲንግ አገልግሎት፣ የጥሪ ማዕከል አገልግሎት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ተጨማሪ አገልግሎቶች፣ የውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች እና የውጭ የቴሌኮሙኒኬሽን መገልገያዎች ተከላ እና ጥገና ሥራዎች ላይ መሰማራት ይችላል፡፡

ለ) የዳታ ማዕከል አገልግሎት ፈቃድ የወሰደ ባለፈቃድ የሆስቲንግ አገልግሎት፣ የጥሪ ማዕከል አገልግሎት እና የቴሌኮሙኒኬሽን ተጨማሪ አገልግሎቶች መስጠት ላይ መሰማራት ይችላል፡፡

ሐ) የሁሉን አቀፍ አገልግሎት ተደራሽነት ግዴታ ያለበት የህዝብ ብሔራዊ የፖስታ አገልግሎት ፈቃድ የወሰደ ባለፈቃድ ዓለም አቀፍ የፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት እና የሀገር ውስጥ ፈጣን መልዕክት (ኩሪየር) አገልግሎት መስጠት ላይ መሰማራት ይችላል፡፡

## 20. የቪሳት እና የመገናኛ ሬዲዮ መሣሪያዎች ፈቃድ

ባለሥልጣኑ ለሚሰጠው የቪሳት እና የመገናኛ ሬዲዮ መሣሪያዎች ፈቃድ የሚከተሉትን ክፍያዎች የሚያስከፍል ይሆናል፡፡

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን መሳሪያው ስም | መለኪያ | የፈቃድ ክፍያ | ዓመታዊ የፈቃድ እድሳት ክፍያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የግል ቪሳት መሣሪያ ፈቃድ (ለዓለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ወይም ኤምባሲ ወይም የውጭ ሀገር ኩባንያ) | በመሣሪያ ብዛት | $ 20,000.00 (በአሜሪካ ዶላር) | $ 20,000.00 (በአሜሪካ ዶላር) |

| ተ/ቁ | የኮሙኒኬሽን መሳሪያው ስም | መለኪያ | የፈቃድ ክፍያ | ዓመታዊ የፈቃድ እድሳት ክፍያ |
|---|---|---|---|---|
| 2 | የግል ቪሳት መሣሪያ ፈቃድ (ለመንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆነ የሀገር ውስጥ ኩባንያ) | በመሣሪያ ብዛት | 600,000.00 (በብር) | 600,000.00 (በብር) |
| 3 | የግል መገናኛ ሬዲዮ መሣሪያ ፈቃድ | በቀረበ ማመልከቻ | 500.00 (በብር) | 500.00 (በብር) |

## ክፍል አምስት

## የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥሮች ክፍያ

### 21. የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር የክፍያ ዓይነት እና መጠን

1/ ባለሥልጣኑ ለሚመድበው የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር የምደባ እና ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ የሚያስከፍል ይሆናል።

2/ ባለሥልጣኑ የምደባ እና ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ የሚያስከፍለው ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡-

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት/ (በብር) | ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ/ አገልግሎት ላይ በዋሉ (Active) ቁጥሮች ብዛት/ (በብር) |
|---|---|---|---|
| 1 | ለሞባይል፣ ከማሽን ወደ ማሽን አይኦቲን ጨምሮ እና ለቮይስ ኦቨር አይፒ አገልግሎት የሚውሉ ቁጥሮች | 0.30 | 0.30 |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት/ (በብር) | ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ/ አገልግሎት ላይ በዋሉ (Active) ቁጥሮች ብዛት/ (በብር) |
|---|---|---|---|
| 2 | ለመደበኛ ስልክ አገልግሎት የሚውሉ ቁጥሮች | 0.10 | 0.10 |
| 3 | ብሔራዊ የሲግናሊንግ ፖይንት ኮድ (NSPC) | 10,000.00 | 10,000.00 |
| 4 | ዓለም አቀፍ የሲግናሊንግ ፓይንት ኮድ (ISPC) | 30,000.000 | 30,000.00 |
| 5 | የሞባይል ኔትዎርክ ኮድ (MNC) | 30,000.00 | 30,000.00 |
| 6 | የኔትዎርክ ቀለም ኮዶች (NCC) | 1,000.00 | 1,000.00 |
| 7 | የሲም ሰጪ መለያ ቁጥሮች (IIN)/ሲም ሄደር | 7,500.00 | 7,500.00 |
| 8 | የዳታ ኔትዎርክ መለያ ኮዶች (DNIC) | 1,000.00 | 1,000.00 |
| 9 | የአገልግሎት አቅራቢ ምርጫ/የቅድመ ምርጫ ኮዶች | 1,000.00 | 1,000.00 |
| 10 | **ዩኤስኤስዲ (USSD) ኮዶች** | | |
| 10.1 | 3 ዲጂት ዩኤስ ኤስ ዲ ኮዶች (ምሳሌ*123#) | 3,000.00 | 3,000.00 |
| 10.2 | 4 ዲጂት ዩኤስ ኤስ ዲ ኮዶች (ምሳሌ*123*4#) | 1,500.00 | 1,500.00 |
| 10.3 | 5 ዲጂት ዩኤስ ኤስ ዲ ኮዶች እና ከዛ በላይ (ምሳሌ*123*45#) | 750 | 750 |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት/ (በብር) | ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ/ አገልግሎት ላይ በዋሉ (Active) ቁጥሮች ብዛት/ (በብር) |
|---|---|---|---|
| 11 | **ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ አጭር ቁጥሮች** | | |
| 11.1 | **ፕላቲኒየም**<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 5 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 44444)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 5 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 23456)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 4444)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 2345)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 444)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተከታታይ አሃዞች (ለምሳሌ 234) | 500.00 | 3,000.00 |
| 11.2 | **ወርቅ**<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 1 4444)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 4 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 7 1234)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 2 ጥንድ ተደጋጋሚ አሃዞች | 500.00 | 2,500.00 |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት/ (በብር) | ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ/ አገልግሎት ላይ በዋሉ (Active) ቁጥሮች ብዛት/ (በብር) |
|---|---|---|---|
| | ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 11 444)<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 2 ጥንዶች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 1 34 34፣ 1 22 55)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁትር ሆኖ 2 ጥንዶች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 34 34)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ ጥንድ ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 22 55)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተከታታይ አሃዞች ያሉት ቁጥር (2 456)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 2 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 3 44) | | |
| 11.3 | **ብር**<br>• ባለ 5 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 13 444)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ 3 ተደጋጋሚ አሃዞች (ለምሳሌ 3444)<br>• ባለ 4 አሃዝ ቁጥር ሆኖ በተመሳሳይ አሃዝ የሚጀምር እና የሚያልቅ እና ጥንድ | 500.00 | 2,000.00 |

| ቁጥር | የቁጥር ሃብት ዓይነቶች | የምደባ ክፍያ/ በተመደበ ቁጥር ብዛት/ (በብር) | ዓመታዊ የመጠቀሚያ ክፍያ/ አገልግሎት ላይ በዋሉ (Active) ቁጥሮች ብዛት/ (በብር) |
|---|---|---|---|
| | ተደጋጋሚ አሃዞች ያሉት ቁጥር (ለምሳሌ 3443፣ 5005)<br>• ባለ 3 አሃዝ ቁጥር ሆኖ በተመሳሳይ አሃዝ የሚጀምሩ እና የሚያልቁ ቁጥሮች (ለምሳሌ 343፣ 505) | | |
| 11.4 | **ነሐስ**<br>• ከላይ የተገለጹት ምድቦች ላይ የማይካተቱ ባለ 5፣ 4 እና 3 አሃዝ አጭር ቁጥሮች | 500 | 1,500.00 |
| 12 | የድንገተኛ እና የደህንነት አገልግሎቶች ቁጥሮች (ፖሊስ, የእሳት አደጋ እና የድንገተኛ ህክምና አገልግሎቶች, የህጻናት እርዳታ መስመር) | ነጻ | ነጻ |
| 13 | ለደንበኛ አገልግሎት እና ለሂሳብ አከፋፈል ተዛማጅ ጥያቄዎች ባለ 3-አሃዝ የተለመዱ የኔትዎርክ ኮዶች | ነጻ | ነጻ |
| 14 | የቁጥር ማዛወር ቅድመ-ቅጥያ ኮዶች/ የቁጥር ማዛወር የራውቲንግ ኮዶች (NPRC) | ነጻ | ነጻ |
| 15 | ማህበራዊ፣ ሰብአዊ እና ህዝባዊ አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ ለመንግስት አገልግሎት የተመደቡ ቁጥሮች:: | ነጻ | ነጻ |

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 22. ፈቃድ ስለማሳደስ

1/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን ወይም ባለፈቃዱ ካስመዘገበው የበጀት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 6 ወራት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

2/ የቪሳት መሣሪያ ፈቃድ የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ሲሆን የፈቃድ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

3/ የመገናኛ ሬዲዮ መሣሪያ ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን ባሉት 6 ወራት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

4/ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሣሥ 30 ቀን ባሉት 6 ወራት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

### 23. የክፍያ ጊዜ እና የክፍያ ሁኔታዎች

1/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች ዓመታዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መጠቀሚያ ክፍያ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ቀን ባሉት ሶስት (3) ወራት ውስጥ መክፈል አለባቸው፡፡

2/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች ዓመታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር መጠቀሚያ ክፍያ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ቀን ባሉት ሶስት (3) ወራት ውስጥ መክፈል አለባቸው፡፡

3/ ዓመታዊ አስተዳደራዊ ክፍያ በየበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ቀን ባሉት ሶስት (3) ወራት ውስጥ መከፈል አለበት፡፡

4/ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች አዲስ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ በሚሰጥበት ወይም የቁጥር ምደባ በሚደረግበት ጊዜ የበጀት ዓመቱ ሊጠናቀቅ ስድስት (6) ወር ወይም ከስድስት (6) ወር በታች ከቀረው ለፈቃድ እና ለምደባው የሚከፈለው መጠን ለሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ወይም ለቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ምደባ ከተወሰነው ክፍያ ግማሹን ይሆናል፡፡

5/ የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ የአዲስ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ሲቀርብ የሚከፈል ሲሆን አመልካቹ የፈቃድ መስፈርቶችን ሳያሟላ ሲቀር እና የተጠየቀው ፈቃድ ባይሰጥ ለፈቃድ ማመልከቻ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ አይደረግም፡፡

6/ ባለሥልጣኑ ለሚሰጣቸው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እና የሬጉላቶሪ አገልግሎቶች ክፍያ የሚፈጸመው በኢትዮጵያ ብር ይሆናል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 6 የተደነገገው ቢኖርም የግል ቪሳት መሣሪያ ፈቃድ፣ የዓለም አቀፍ የሳተላይት የግል ሞባይል ግንኙነት አገልግሎት ፈቃድ እና የግል ኔትዎርክ እና እርስበርስ የሚገናኙ የተጠቃሚዎች ግሩፕ ፈቃድ አመልካች ወይም ባለፈቃድ ዓለም አቀፋዊ ወይም አህጉራዊ ወይም ኤምባሲ ወይም የውጭ ሀገር ኩባንያ ከሆነ የፈቃድ እና የዕድሳት ክፍያ በአሜሪካ ዶላር የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 24. ቅጣት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 ንዑስ-አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰው የፈቃድ ማሳደሻ ጊዜ ውስጥ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃድ ፈቃዱን ካላሳደሰ ከጥር 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ላለው ጊዜ ከፈቃድ ማሳደሻው በተጨማሪ ፈቃድ ማሳደሱ ለዘገየበት ለጥር ወር ብር 2,500 ብር (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) እና ለሚቀጥለው እያንዳንዱ ወር ብር 1,500 ብር (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ቅጣት በመክፈል ፈቃዱን ያሳድሳል፡፡

2/ በቅጣት የማሳደሻ ጊዜ ውስጥ ያላሳደሰ ማንኛውም የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለፈቃድ በቅጣት የማደሻው ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከፈቃድ ማሳደሻው በተጨማሪ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) በመክፈል ፈቃዱን ማሳደስ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ያልታደሰ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ያንኑ ፈቃድ መልሶ ማውጣት የሚቻለው በቅጣት የማሳደሻ ጊዜው ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ያለምንም ተጨማሪ ቅጣት እንደ አዲስ ፈቃድ በመውሰድ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3፣ እና 4 እና አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ እና 3 ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ተገቢውን የቪሳት መሣሪያ ፈቃድ ዕድሳት፣ የመገናኛ ሬዲዮ መሣሪያ ፈቃድ ዕድሳት፣ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ፈቃድ ዕድሳት ወይም ዓመታዊ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መጠቀሚያ፣ ዓመታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር መጠቀሚያ እንዲሁም የሚፈለግበትን አስተዳደራዊ ክፍያ ያልፈጸመ ማንኛውም ባለፈቃድ ከዚህ በታች የተጠቀሰው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡-

ሀ) ለመጀመሪያው አንድ ወር የአጠቃላይ ክፍያው 1%፤

ለ) ለሁለተኛው ወር የአጠቃላይ ክፍያው 2%፤

ሐ) ለሶስተኛው ወር የአጠቃላይ ክፍያው 5% እንዲከፈል ይደረጋል፤

መ) ባለፍቃዱ ከሶስት (3) ወራት በላይ ፈቃዱን ሳያሳድስ ከቆየ ወይም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም መጠቀሚያ ክፍያ፣ የቁጥር መጠቀሚያ ክፍያ እንዲሁም ማንኛውንም የሚጠበቅበትን አስተዳደራዊ ክፍያ ሳይፈጽም ከቀረ፤ ባለስልጣኑ ፈቃዱን እንደ ሁኔታው ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፤

## 25. የተሻሩ መመሪያዎች

1/ የቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 1/1997 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ የግል ቪሳት ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 6 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

3/ የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 6 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 26.ማሻሻያ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለሁሉም ባለፈቃዶች በቅድሚያ በማሳወቅ እና ከአዋጁ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የባለድርሻ አካላት የምክክር ሂደት በማካሄድ በማንኛውም ጊዜ ይህን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

## 27. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ድህረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣ መስከረም 2017 ዓ.ም**

**ባልቻ ሬባ (ኢንጂነር)**

**የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**